# የኢትዮጵያ

# ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)

# ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL (EHRCO)


**አስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫ**

## በኢሰመጉ ፅ/ቤት ላይ የተፈጸመ ህገ-ወጥ ተግባርን አስመልክቶ ከኢሰመጉ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

የካቲት 06/2015 ዓ.ም

**የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ)** ላለፉት ሶስት አስርት ዓመታት በአገሪቱ ያለው የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ እንዲሻሻል የበኩሉን ዘርፈ ብዙ አስተዋጾ ሲያደርግ የቆየ መንግስታዊ ያልሆነ ከማናቸውም አድልዎ ነፃና ገለልተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋም ነው፡፡ ይሁን እንጂ ስራውን ለማሳለጥ ሊደረግለት ከሚገባቸው መልካም አጋጣሚዎች ይልቅ በርካታ ጫናዎች እንደ ግድያ፣ ድብደባ፣ ህገ-ወጥ እስራት፣ ዛቻና ማስፈራራት እንዲሁም ሰራተኞችና አባላት ሀገር ለቀው እንዲሰደዱ ሲደረግበት ቆይቷል፡፡ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጫናዎቹ እየተደጋገሙ የመጡ ሲሆን ለዚህም ማሳያነት በኢሰመጉ ጋምቤላ ቅርንጫፍ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ላይ የደረሱ ዛቻዎችና ማስፈራራቶች፣ በ24/03/2015 ዓ.ም አዲስ አበባ ልደታ አካባቢ በሚገኘው የኢሰመጉ ማዕከላዊ ቀጠና ጽ/ቤት አቤቱታ ለማቅረብ የመጡ 28 አቤቱታ አቅራቢዎች ምንም እንኳን ሌሎች ተቋማት ላይ አቤቱታቸውን አቅርበው ሲወጡ ምንም አይነት ህገ-ወጥ ድርጊት ባይፈጸምባቸውም ነገርግን ወደ ኢሰመጉ መጥተው አቤቱታቸውን አቅርበው እንደወጡ በኢሰመጉ ጽ/ቤት በር ላይ 22 አቤቱታ አቅራቢዎችን የመንግስት የጸጥታ አካላት አቤቱታ አቅራቢዎች ላይ የማስፈራሪያ መልእክት ለማስተላለፍ በሚመስል መልኩ ማሰራቸው እንዲሁም በኢሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ላይ ከተለያዩ የመንግስት አካላት በስልክ የሚፈጸሙ ዛቻዎችና ማስፈራሪያዎች በመንግስት የፀጥታ አካላት በኩል በኢሰመጉ ላይ እየተፈጸሙ ያሉ የተለያዩ ጫናዎች የሚጠቀሱ ድርጊቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ታህሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም ለኢሰመጉ በቀረበ አቤቱታ መነሻነት የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታን ለማጣራት ስራ የሄዱ አራት የኢሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ለስምንት ቀናት ያለ አግባብ በሸገር ከተማ አስተዳደር ገላን ጉዳ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ታስረው ቆይተው በዋስ መለቀቅን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በኢሰመጉ ላይ የሚፈጸመው ልዩ ልዩ ጫና ከመቀነስ ይልቅ ዳራውን እያሰፋ በመሄድ ኢሰመጉ በቅርቡ በአዲስ መልክ የከፈተው በኮሜርስ አካባቢ በሚገኘው የምርመራ ክፍል ቅዳሜ የካቲት 4 ቀን 2015 ዓ.ም ከሰዓት 9፡40 ሰዓት አካባቢ ለግዜው ማንነቱ ተለይቶ ባልታወቀ አካል የጋራ መግቢያ በር ቁልፍ በመስበር የሌሎች ከጎን ተያይዘው ያሉ ቢሮዎች ሳይነኩ የኢሰመጉ ቢሮ ቁልፍ ተሰብሮ በቢሮ ውስጥ ከሚገኙ ንብረቶች መካከል ተለይቶ የክፍሉ ኃላፊ መሳቢያ ቁልፍ በመስበር በውስጡ የነበረ ላፕቶፕ ኮምፒውተር ተወስዷል፡፡ በጽ/ቤቱ ውስጥ በወቅቱ የነበሩ ሌሎች ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተርና የጽ/ቤት ንብረቶች ያልተወሰዱ ሲሆን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች፣ ክትትልና ሪፖርት መምሪያ ኃላፊን ላፕቶፕ ኮምፒውተር ብቻ ተመርጦ መወሰዱ ጉዳዩ ተራ ሌብነት እንዳልሆነ በግልፅ መረዳት ይቻላል፡፡ በተለይም በተወሰደው ላፕቶፕ ኮምፒውተር ውስጥ ካሉት በርካታ በሂደት ላይ ያሉ የምርመራ ጉዳዮች አንፃር ድርጊቱ የተጠና መሆኑንና ተራ ስርቆት እንዳልሆነ መረዳት የሚቻል ሲሆን ይህም ድርጊት ላፕቶፕ ኮምፒውተሩ ከያዛቸው መረጃዎች ሚስጥራዊነት አንጻር ኢሰመጉን በእጅጉ ያሳስበዋል። ይህ ብርበራ በሚመስል ሁኔታ በኢሰመጉ ላይ የተፈጸመ የቢሮ ሰበራ ከእዚህ ቀደም በተመሳሳይ በዋናው ጽ/ቤት እንዲሁም ሀዋሳ በሚገኘው የኢሰመጉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ላይ የተፈጸመ ድርጊት ሲሆን ይህም ኢሰመጉ በተከታታይ ጫና ውስጥ እንዳለ በግልጽ የሚያሳይ ህገ-ወጥ ድርጊት ነው፡፡ በኢሰመጉ የምርመራ ክፍል ቢሮ ላይ የተፈጸመውን የቢሮ ሰበራ ኢሰመጉ

በአካባቢው ለሚገኝ ፖሊስ ያመለከተ ሲሆን ፖሊስም ጉዳዩን እየተከታተለው ይገኛል ስለሆነም ኢሰመጉ የፖሊስን የመጨረሻ የምርመራ ውጤት በመጠባበቅ ላይ ያለ ሲሆን ይህንን የምርመራ ውጤት ወደፊት ይፋ የሚያደርግ ይሆናል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢሰመጉ ሰራተኞች፣ አባላትና የድርጅቱ ጽ/ቤቶች ላይ ተጠናክረው እየተፈጸሙ ያሉ ልዩ ልዩ ህገወጥ ተግባራትና ጫናዎች ድርጅቱ በገለልተኝነት እና በቆራጥነት እየሰራው ያለውን የሰብዓዊ መብቶች የማስከበር፣ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ክትትልና ምርመራ ስራ ለማደናቀፍና የተቋሙ ባለሙያዎች ስራቸውን እንዳይሰሩ ብሎም ደህንነታቸውን አደጋ ውስጥ ለመክተት ታቅዶበት በተደጋጋሚ እየተደረገ ያለ ድርጊት መሆኑን ኢሰመጉ ያምናል፡፡

## ተያያዥ የህግ ግዴታዎች፡

የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ከሚሰሩት ስራ እና ስራውን ተከትሎ ከሚመጡ ጥቃቶች ይጠበቁ ዘንድ እነዚህ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ልዩ ጥበቃ እንደሚያስፈልጋቸው የተባበሩት መንግስታት በተደጋጋሚ በሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾችን ሁኔታ በሚከታተሉት ልዩ ዘጋቢ (Special Rapporteur on the situation of human rights defenders ) በኩል ሲገልጽ ቆይቷል፡፡ የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተረጋገጡ ሰብዓዊ መብቶችን እና መሰረታዊ ነጻነቶችን ለማስተዋወቅ እና ለመጠበቅ የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችን፣ ቡድኖችን እና የህብረተሰብ አካላትን መብት እና ኃላፊነት ለመወሰን የወጣው ድንጋጌ፣ ድንጋጌ ቁጥር 53/144 በመግቢያው ላይ እንዲሁም በአንቀጽ 2፣ 9 እና 12 ላይ ሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን ደህንነት የመጠበቅ እና የማስጠበቅ ኃላፊነት የመንግስት መሆኑን ይገልጻል፡፡ ምንም እንኳን ይህ መግለጫ በሀገራት ላይ አስገዳጅ ነው ማለት ባይቻልም በውስጡ አካትቶ የያዛቸው ድንጋጌዎች ማለትም ለሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች የሰጣቸው መብቶች የተውጣጡት በመንግስት ላይ ሰብዓዊ መብቶችን የማስከበር ኃላፊነት ከሚጥሉ የተለያዩ ገዢ ከሆኑ ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች በመሆኑ በውስጡ የተካተቱ መርሆዎች ገዢ ይሆናሉ፡፡

የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ መብቶች ኮሚቴ በ 2015 ዓ.ም ባወጣው ጥቅል አስተያየት (General Comment) 26 አንቀጽ 55 ላይ አባል ሀገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ለሚሰሯቸው ስራዎች ጥበቃን ማድረግ ይችሉ ዘንድ ሊወስዷቸው ይገባል ብሎ ካስቀመጣቸው ነጥቦች መካከል የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች የሚሰሩት ስራ ጥቅሙንና ህጋዊነቱን በከፍተኛ የመንግስት አካል ይፋዊ እውቅና መስጠት እንዳለበት እንዲሁም በእነሱ ላይ የሚደርስ ማንኛውም አይነት ጥቃትና ማስፈራራት ተቀባይነት እንደሌለው መንግስት ቁርጠኝነትን ማሳየት እንዳለበት ይገልጻል፡፡

## የኢሰመጉ ጥሪ፡

- መንግስት በኢሰመጉ ላይና በተቋሙ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ላይ እየደረሱ ያሉ ዘርፈ ብዙ ጫናዎችን በአስቸኳይ እንዲያስቆም፣ ለዚህም ማረጋገጫነት በመንግስት የፍትህና የጸጥታ አካላት በኢሰመጉ ላይ ያለአግባብ የሚደርሱ ጫናዎችን በመከላከል፣ በማስቆም ብሎም በፍትህ አግባብ በመጠየቅ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ረገድ ያለበትን የማስከበር ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ፣
- የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ መብቶች ኮሚቴ ጥቅል አስተያየት እንደሚገልጸው መንግስት በሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ላይ የሚደርስ ማንኛውም አይነት ጥቃትና ማስፈራራት ተቀባይነት እንደሌለው ቁርጠኝነቱን እንዲያሳይ እንዲሁም ለኢሰመጉ ስራዎች ተገቢውን እውቅና እንዲሰጥ፣
- የፌደራል እና የክልል መንግስታት እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋማትና በአጠቃላይ የሲቪል ማህበራት በአገሪቱ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታና ለህግ የበላይነት መስፈን የሚያደርጉትን የማይተካ ከፍተኛ አስተዋጾ በመገንዘብ እና እውቅና በመስጠት ከሚሰሩት ስራ ጋር ተያይዞ እየደረሱባቸው ያሉ ጫናዎችን በተመለከተ አስፈላጊውን ጥበቃ እና የህግ ከለላ እንዲሰጡ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ